# በአዲስ  አበባ ከተማ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን

## ጉለሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

### የተሻሻለ የትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች መረጃ መመዝገቢያ  እና አገልግሎት አሰጣጥ ሲስተም(ቴክኖሎጂ) ምርጥ ተሞክሮ መቀመርና ማስፋት

**ግንቦት 2016 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

# የተሻሻለ የትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች መረጃ መመዝገቢያ እና አገልግሎት አሰጣጥ ሲስተም(ቴክኖሎጂ) ምርጥ ተሞክሮ መቀመርና ማስፋት

## የቅመራ ተሳታፊዎች

1. ስዩም ጀንዶ
2. ጥበበ ዳንኤል
3. ነስሩ መሃመድ
4. ኅይቶም አስፋው
5. ብሩክ በለጠ
6. ሃይማኖት አዳነ

## ማውጫ

1. መግቢያ 1
1.1. የተቋሙ ዳራ 2
1.2. የዚህ ምርጥ ተሞክሮ ቅመራና ማስፋት አጠቃላይ ዓላማ 3
1.3. የምርጥ ተሞክሮ ቅመራና ማስፋት ዝርዝር አላማዎች 3
1.4. የምርጥ ተሞክሮ ቅመራና ማስፋት አስፈላጊነት 3
2. የተቋሙ ነባራዊ ሁኔታ ትንተና 5
2.1. ተቋሙ ወደ ለውጥ ከመምጣቱ በፊት የነበሩ ጠንካራ ጎኖች 5
2.2. በተቋሙ ወደ ለውጥ ከመምጣቱ በፊት የነበሩ ደካማ ጎኖች 5
2.3. በተቋሙ ከለውጡ በፊት የነበሩ አስቻይ ሁኔታዎች 6
2.4. ከለውጡ በፊት የነበሩ ስጋቶች 6
3. በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ለውጥ ለማምጣት የነበረው አስተሳሰብ 7
3.1. ቅድመ ለዉጥ አስተሳሰብ 7
3.1.1. በአመራሩ ዘንድ የነበረ ለዉጥ አስተሳሰብ 7
3.1.2. በመረጃ ባለሙያዎች ዘንድ የነበረ ለዉጥ አስተሳሰብ 7
3.1.3. በተገልጋዮች ዘንድ የነበረ ለዉጥ አስተሳሰብ 7
3.2. በለዉጥ ትግበራ ሂደት የነበረ አስተሳሰብ 7
3.2.1. አመራሩ ዘንድ የነበረ አስተሳሰብ 7
3.2.2. የመረጃ ባለሙያዎችዘንድ የነበረ አስተሳሰብ 7
3.2.3. ተገልጋዮች ዘንድ የነበረ አስተሳሰብ 7
3.3.ድህረ ለዉጥ አስተሳሰብ 8
3.3.1. ድህረ ለዉጥ በአመራሩ ዘንድ የነበረ የአስተሳሰብ 8
3.3.2. የመረጃ ባለሙያዎች ዘንድ የነበረ የ አስተሳሰብ 8
3.3.3. ተገልጋዮች ዘንድ የነበረ የ አስተሳሰብ 8
4. ከምርጥ ተሞክሮው የተገኘው ውጤት 9
4.1. ከተገልጋይ አንጻር 9
4.2. ከመረጃ ባለሙያዎች አንጻር 9
4.3. ከባለድርሻ አካላት አንጻር 9
4.4. ከባለስልጣን መ/ቤቱ አንጻር 9
5. ከምርጥ ተሞክሮ የተገኘው ስኬት 10
5.1. በተቋሙ ስኬት የተገኘበት ዝርዝር ሂደት 10
5.2. የበለፀገውን ሲስተም ለመተግበር ያጋጠሙ ማነቆዎች 11
5.3. የበለፀገውን ሲስተም ለመተግበር ያጋጠሙ ማነቆዎች የተፈቱበት አግባብ 11
6. የደንብ ተላለፊ ስሲተም በማበልፀግ የተሳሳፉ አካላትና የተጫወቱት ሚና 12
6.1. የመንገድ ትራፊክ ደንብ ማስከበር ዳይሬክተር የነበረው ሚና 12
6.2. የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጇ የነበራቸው ሚና 12

6.3. የባለሙያ ሚና ........ 12
6.4. የሌሎች ባለድርሻ አካላት ሚና ........ 12
7. ተሞክሮውን እውን እንዲሆን ሊከናወኑ የሚገቡ ተግባራት ........ 13
7.1. የበለፀገው ሲስተም ክፍሎች ........ 13
7.1.1. ባለቤት (Owner) ፡ ........ 13
7.1.2. አዘጋጅ (Editors) ፡ ........ 13
7.1.3. አስተያየት ሰጪ (Commentator) ፡ ........ 14
7.1.4.ለማንበብ ብቻ የተፈቀደ (Read-only) ፡ ........ 14
7.2. የሲስተሙ ተጠቃሚዎች ተግባርና ሀላፊነት ........ 14
7.2.1. የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ዝርዝር ተግባራት ........ 14
7.2.2. የመንገድ ደህንነት ግንዛቤ እና ደንብ ማስከበር ዳይሬክተር (Owner) ፡ ........ 14
7.2.3. የትራፊክ ደንብ ማስከበር ቁጥጥር ቡድን ስራዎች አስተባባሪ (Editors)፡ ........ 14
7.2.4. የዳታ ኢንኮደር ባለሙያ ተግባራት (Commentator) ........ 15
7.2.5. የትራፊክ ተቆጣጣር ባለሙያዎች ተግባራት ........ 15
8. ሌሎችተቋማት ሊማሩትየሚገባ ቁም ነገር ........ 16
9 መደሚደምያ እና ማጠቃለያ ........ 17
9.1 የምርጥ ተሞክሮ ቀማር ኮሚቴ ምክረ ሀሳብ ........ 17
9.2.-መደሚደምያ ........ 17
9.3- ማጠቃለያ ........ 18

## ክፍል አንድ

### 1. መግቢያ

በ21ኛዉ ክ/ዘመን አለም ዉስጥ አንድ ሀገር አለም የደረሰበትን ቱክኖሎጅ ተጠቅማ ከሌላዉ ሀገር ጋር መወዳደር ካልቻለች ኢኮኖሚያዊ፤ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ህልዉናዋ ጥያቄ ምልክት ዉስጥ እንደሚገባ አያጠያይቅም፡፡አንድ ሀገር በቴክኖሎጂ ያላት ብቃት ደግሞ በእያንዳንዱ ተቋም ያለው የቴክኖሎጂ እና ቴክኖሎጂን የመጠቀሚ ችሎታና ብቃት ያለው የሰው ሀይል እንዲሁም በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ያመጣው ለውጥ፣ውጤት እና ስኬት ብልሹ አገልግሎት፣ሌብነት፣የመልካም እስተዳደር ችግር እና በመረጃ አየያያዝና ተደራሽነት ዙሪያ የሚታ ዩ ችግሮች በመቅረፍ የተገልጋይን እርካታ በማሳደግ በመንግስትና በህዝብ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ በመሆኑ በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት መስጠት ወቅቱ የሚፈልገው ግድ የሆነበት ጊዜ ነው፡፡

በአገራችን ብሎም በከተማችን የተጀመረውን የለውጥ ስራ በተፈለገው ፍጥነትና ጥራት ለመተግበር ያስችል ዘንድ የመንግስት ተቋማት በስታራቴጂክ እቅድ ትግበራ\ ዙሪያ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን በማስባሰብና\ በመቀመር ወደ ለሌሎች እንድሰፋ በማድረግ የተቋማት አገልግሎት አሰጣጣቸውን በማሻሻል እና የውስጥ አሰራር ስርዓትን በማዘመን የአገልግሎት አሰጣጡን ውጤታማና ቀልጣፋ በማደረግ የህብረተሰብን እርካታ ማሳደግ ወቅቱ የሚፈልገው በመሆኑ መንግስት ለቴክኖሎጂ በሰጠው ትኩረት በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ አገልግሎት ሰጪ የመንግስት ተቋማት በትኩረት መስራት ተጀመረ ቆይቷል፡፡ከዚህ አንፃር በከተማ አስተዳደራችን የቤንችማርኪንግ ትግበራ ከዚህ በፊት ያልነበረ ሲሆን በተሞክሮ ቅመራና ማስፋት ረገድም ከ2006ዓ.ም ጀምሮ በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመለየት፣በመቀመርና በማስፋት የተጀመሩ ጅምር ስራዎች ቢኖሩም ከውጤታማነት አንፃር ሰፊ ክፍተቶች ይሰታዋላሉ፡፡

ከዚህ ቀደም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተቋማት የሚቀምሯቸው ተሞክሮዎች ወደሌሎች ተቀምረው እንዲሰፉ ከማድረግ በዘለሴ ስራ ክፍሎች በተቋማቸው ከሚገኙ ውጤታማ ስራ ክፍሎች ተሞክሮዎችን በመውሰድ የአፈፃፀም አቅማቸውን ማሳደግ እንዲችሉ ማድረግ አንደኛው ትኩረት ነው፡፡ይህ እስካሁን በከተማችን እየተተገበረ የሚገኘው የእውቀት አሰተዳደር ስርዓት ወደ ተግበር የሚያስገባ እንደሚሆን ታምኖበታል፡፡ ተቋማት ክፍተታቸውን በመፈተሽ ውጤታማነታቸው በተለየያዩ መንገዶች ከተጋረጠባቸው ተመሳሳይ ወይም ልዩ ባህርይ ያላቸው ተቋማትን ቤንችማርክ በማድረግ ለውጤታማነታቸው መሰረት የሆነውን አሰራር ቤንችማርክንጉን የወሰዱ ተቋማት በራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ በመተግበር በውጤታማነትና አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ላይ መሻሻል እንዲያመጣ ማድረግን ታሳቢ ያደረገ ነው

በሌላ መልኩ ምርጥ ተሞክሮ መለየት፣መቀመርና ማስፋት በከተማችን በሚገኙ ተቋማት ቤንችማርክ የተደረጉ ልምዶችንና የራስን አፈፃፀም ፈትሾ ተሞክሮን በአጭር ጊዜና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ የተሸሉ ልምዶችን ለሌሎች ተቋማት በማሸሻጋገር አፈፃፀምን ማሻሻልና የአገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን በማረጋገጥ የተገልጋዮችን እንግልት፣ምልልስ፣ብልሹ አገልግሎትን በማስቀረት፣ የመረጃ በቀላሉ አለመገኘትና መጥፋት ችግሮችን በመቅረፍና የተገልጋዮችን እርካት በማሳደግ ረገድ ያለው አስተዋፅኦ የጎላ ነው፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን አገልግሎት አሰጣጥን በቴክኖሎጅ በማዘመን ለህብረተሰቡ በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆን ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡ በዚህም መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን ጉለሌ

ቅርንጫፍ በደንብ ተላላፊ አሽከርካሪ የመረጃ አያያዝና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ለባለጉዳይዮች መጉላላት ምክንያት የሆነውን ችግር ለመቅረፍና የተገልጋይን እርካታ ለማሳደግ የትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች መረጃ መመዝገቢያ ሲስተም በማበልፀግ የትራፊክ ቁጥጥር ባለሙያዎች የእርምት እርምጃ የተወሰደባቸውን የትራፊክ ደንብ ተላለፍ አሽከርካሪ እና ተሽከርካሪ ዝርዝር መረጃ በተሟላ መልኩ መመዝገብ ማስተዳደር ባለቻሉ ምክንያት በመረጃ መጥፋት በህብረተሰብ ላይ የሚደርሰውን እንግልትና ብልሹ የአገልግሎት አሰጣጥና ሌብነት በማስቀረት በህብረተሰቡን እርካታ ለማሳደግ የበለጸገ ሲስተም ነዉ፡፡

## 1.1. የተቋሙ ዳራ

አዲስ አበባ ከተማ የፌደራል መንግስት ዋና ከተማና የተለያዩ ማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚገኙባት ከመሆኗ በተጨማሪ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ዓለም-አቀፍ ተቋማት መቀመጫ በመሆን እያገለገለች ትገኛለች፡፡ የከተማው ነዋሪ ህዝብ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ ዕድገቱ እየጨመረና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፍላጎቱን ለማሟላት በሚያደርገው እንቅስቃሴም የትራንስፖርት አገልግሎት ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዝበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡

የከተማዋን የማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ተከትሎ እየተፈጠረ ያለው የሞተር ተሽከርካሪ ቁጥር እና እንቅስቃሴ መጨመር፣ የትራፊክ ፍሰቱ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አለመሆንና የተጠናከረ የትራፊክ ማኔጅመንት ትግበራ ሥርዓት አለመኖሩ ከተማችንን ዘርፈ ብዙና ውስብስብ ለሆኑ ችግሮች እንድትጋለጥ አድርጓታል፡፡ በከተማ አስተዳደሩ ዋና ዋና መንገዶች ላይ የሚደረጉትን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ስንመለከት የእግረኞች ተገቢ በሆነ መልኩ መንገዶችን አለመጠቀም፣ በእግረኞችም ሆነ በተሽከርካሪዎች ዘንድ የመንገድ ትራፊክ ደንብና ሥርዓትን ጠብቆ አለመጓዝና አለማሽከርከር፣ ሕገ-ወጥ እና ያለበቂ ጥናት ሥራ ላይ የዋሉ የመንገድ ላይ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታዎች (Road Parking) መበራከት፣ በሥርዓትና በበቂ የተዘጋጁ የተሽከርካሪ ማቆሚያና የትራንስፖርት ተገልጋዮች መጠለያና ማረፊያ ሥፍራዎች እንዲሁም ምቹ የእግረኛ መንገዶች አለመኖር ከሁሉም በላይ የመንገድ ትራፊኩን የሚያሳልጥ ሥርዓት አለመዘርጋቱ ከፍተኛ የሆነ የትራፊክ መጨናነቅና፣ የተሽከርካሪ አደጋ መንስዔ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የትራፊክ ማኔጅመንት አሰራርና ዘመናዊ የትራፊክ መረጃ ማእከል ባለመኖሩ የሚፈጠረው የትራፊክ ችግር በአብዛኛው አምራች በሆነው የህበረተሰብ ክፍል ላይ በሚያደርሰው የህይወትና የአካል ጉዳት ፣ የንብረት ውድመትና በምርታማነት ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ከፍተኛ ሲሆን በትራፊክ መጨናነቅ ምክንያት የሚፈጠረው የጊዜ ብክነትም በአጠቃላይ ኢኮኖሚው ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እያሳደረ በመምጣቱ ምክንያት የአዲስ አበባ ከተማ ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በ2007 የከተማ አስተዳደሩን አስፈጻሚ አካላት እንደገና ለማዋቀር ባወጣዉ አዋጅ ቁጥር 43/2007 እራሱን ችሎ እንደ ተቋም የተቋቋመ ሲሆን የተሰጠዉ ስልጣንና ተግባራት 9 ናቸዉ፡፡ ኤጀንሲዉ ወደ ተግባር ከገባ በኋላ በሂደት አዳዲስ ሁኔታዎች በመፈጠራቸዉና በተቋሙ መሸፈን የሚገባቸዉ አዳዲስ አገልግሎቶች እየተፈጠሩ በመምጣታቸዉ የኤጀንሲዉ ስልጣንና ተግባር በአዋጅ ቁጥር 64/2009 እንደገና እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡ እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 74/2011 የኤጀንሲዉ ስልጣንና ተግባር ወደ 17 ያደገ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 84/2016 ኤጀንሲዉ ወደ ባለስልጣን ደረጃ ከማደጉም በተጨማሪ ስልጣንና ተግባራቱም ወደ18 እንዲያድግ ተደርጓል፡፡

በአገራችን ብሎም በከተማችን የተጀመረውን የለውጥ ስራ በተፈለገው ፍጥነትና ጥራት ለመተግበር ያስችል ዘንድ የመንግስት ተቋማት በስታራቴጂክ እቅድ ትግበራ\ ዙሪያ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን በማሰባሰብና\ በመቀመር ወደ ለሌሎች እንድሰፋ በማድረግ የተቋማት አገልግሎት አሰጣጣቸውን በማሻሻል እና የውስጥ አሰራር ስርዓትን በማዘመን የአገልግሎት አሰጣጡን

ውጤታማና ቀልጣፋ በማደረግ የህብረተሰብን እርካታ ማሳደግ ወቅቱ የሚፈልገው በመሆኑ ተቋሙ በትኩረት መስራት የተጀመረ ቆይቷል።

የኤጀንሲዉን የዉስጥ አደረጃጀት ስንመለከት የተቋቋመለትን ዓላማ ለማሳካት ከ2015 በፊት በአምስት ቅርንጫፎች ተዋቅሮ የነበረ ሲሆን አገልግሎት አሰጣጡን ለተገልጋዩ ህብረተሰብ ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ ወደ አስራአንድ ቅርንጫፎች አሳድጓል፡፡ ከእነዚህም አንዱ በአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን ጉለሌ ቅ/ጽ/ቤት ነዉ፡፡

ባለስልጣኑ እንደ አቅጣጫ ካስቀመጠዉ ስልት አንዱ አገልግሎትን በቴክኖሎጅ አስደግፎ መስጠት ሲሆን ለአብነት የሞተር ሳይክል እንቅስቃሴ መቆጣጠሪያ ሲስተም፤ የትራፊክ ቅጣት ማስከፈያ ሲስተም፤ የትራፊክ ስርዓት መቆጣጠሪያ ሲስተም ጥቂቶቹ ናቸዉ፡፡ ቴክኖሎጅ በተቋም ደረጃ ወይም በግለሰብ ደረጃ ሊበለጽግ ይችላል፡፡ ይህ የትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች መረጃ መመዝገቢያ ሲስተም በጉለሌ ቅ/ጽ/ቤት የሲስተም አስተዳደር ባለሙያ በሆነ ሰዉ ፍላጎትና ተነሳሽነት የበለጸገ ሲሆን በተግባርም እየተሰራበት ያለ ሲስተም ነዉ፡፡

### 1.2. የዚህ ምርጥ ተሞክሮ ቅመራና ማስፋት አጠቃላይ ዓላማ

የዚህ ምርጥ ተሞክሮ መቀመርና ማስፋት ዋና ዓላማ በአዲስ አበባ ከተማ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን ጉለሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የመንገድ ትራፊክ ደንብ ተላላፊ አሽከርካሪዎች መረጃ አያያዝ፣ ተገልጋይ ለእንግልት እና ምልልስ እንዲሁም ለሌብነትነና ለብልሹ አገልግሎት አሠጣጥ በር ይከፍት የነበረው ችግር የተፈታበት ምርጥ ተሞክሮ በመቀመር ወደ ሌሎች ተመሳሳይ አገልግሎት በመስጠት ላይ ለሚገኙ ቅርንጫፎች በማሸጋገር የተገልጋይ እርካታ ለማሳደግ ነው፡፡

### 1.3. የምርጥ ተሞክሮ ቅመራና ማስፋት ዝርዝር አላማዎች

1) የቤንችማርኪንግ እውቀት አስተዳደር ስርዓት በተቋማት ውስጥ ለመፍጠር ያስችላል።
2) ምርጥ ተሞክሮ ፅንሰ ሀሳብ ዙሪያ ተቀራራቢ የሆነ ግንዛቤ እና ትግበራ በተቋሙ ውስጥ ይፈጥራል፡፡
3) የቤንችማርኪንግ ትግበራ በማረጋገጥ ቀጣይነት ያለው ተቋማዊ መማማሪና መሻሻል በማምጣት የተገልጋይ እርካታ ለማሻሻል ምርጥ ተሞክሮን ለማስፋት ነው።
4) በጉለሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተገኘ ምርጥ ተሞክሮን ለሌሎች ቅርንጫፎች ከራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣምና በማላመድ የአገልግሎት አሰጣጥን እንዲያሻሽሉ ለማስቻል ነው።
5) ምርጥ ተሞክሮን በማስፋት የቅርንጫፎችን አመራርና ባለሙያዎች አመለካከት፣ እውቀትና ግብአትን ከቴክኖሎጂ ጋር አቀናጅቶ በመጠቀም ውጤት ማምጣት እንደሚቻል ለማሳየት ነው፡፡

### 1.4. የምርጥ ተሞክሮ ቅመራና ማስፋት አስፈላጊነት

- የቅርንጫፉን አገልግሎት አሰጣጥን ቀልጣፋና ጊዜ ቆጣቢ በማድረግና በተገልጋይ ላይ የሚደርሰውን እንግልት በማስቀረት የተገልጋይ እርካታ ለማሳደግ ያስችላል።
- የአመራሩንና የፈፃሚውን ስትራቴጂክ እቅድ አፈፃፀም የተሻለ እንዲሆን ያደርጋል ፣
- ቴክኖሎጂን የመጠቀም ችሎታና ብቃት ያላቸውን ተተኪ ባለሙያዎች ለማፍራት ያስችላል።
- በተቋሙ ብልሹ አሰራርና ሌብነት ለማስቀረት በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎቶች ለመስጠት ያስችላል።
- በተቋሙ ግልፀኝነት እና ተጠያቅነት በመፍጠር ብልሹ አሰራር ለመቅረፍ የሚያስችል ነው።

- ኋላቀር አሰራርን በማስቀረት በቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎት ለመስጠት ያስችላል።
- ተገልጋዮች ስለጠፉባቸዉ መረጃዎች (ሰሌዳ ወይም መንጃ ፈቃድ) በመፈለግ ሚያጠፉትን ጊዜ ለመቀነስ ያስችላል።

# ክፍል ሁለት

## 2. የተቋሙ ነባራዊ ሁኔታ ትንተና

### 2.1. ተቋሙ ወደ ለውጥ ከመምጣቱ በፊት የነበሩ ጠንካራ ጎኖች

- በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት በመስጠት የተገልጋይን እንግልትና ብልሹ አገልግሎት አሰጣጥን ለመቅረፍ ቁርጠኛ የሆነ አመራር መኖር፤
- የተገልጋይ እርካታ ለማሳደግ የአመራሩ ፍላጎትና ተነሳሽነት መኖር፤
- በመረጃ አደራጃጀት፣አያያዝና አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ያሉት ክፍተቶች ተፈትሾ በዳሰሳ ጥናት እንዲለዩ የአመራርና ባለድርሻ አካላት ፍላጎትና ተሳትፎ መኖር
- ቴክኖሎጂን በመጠቀም እውቀትን፣ፍላጎትና ብቃት ያለው ባለሙያ መኖር
- የአግልሎት አሰጣጥ እንድዘምን የአንዳንድ ባለሙያ ተነሳሽነትና ተሳትፎ ጥረት ጠንካራ መሆን
- የዋና በመስሪያቤት ስራ ሀላፊዎች ጠንካራ ሙያዊ ድጋፍ ክትትል በተከታታይነት ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ እደረጉ መኖር
- በቴክኖሎጂ የተደገፈ የእገልግሎት አሰጣጥና መረጃ አያያዝ እንዲኖር የቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሀላፊዎች ፍላጎት እና ተነሳሽነት መኖር

### 2.2. በተቋሙ ወደ ለውጥ ከመምጣቱ በፊት የነበሩ ደካማ ጎኖች

- የእርምት እርምጃ የተወሰደባቸው በደንብ መተላለፍ አሽከርካሪዎች መረጃ በቀላሉ  ማግኘት በሚቻልበት ሁነታ ተደራጅቶ አለመያዝ
- ለትራፊክ  ቁጥጥር የተዘጋጀዉ የኪስ ፓድ ለህጋዊ ስራ ብቻ መዋሉን መቆጣጥር አስቸጋሪ መሆኑ
- በትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች ላይ ጥናታዊ ጽሑፍ ለመስራት ሚያስፈልግ መረጃ በአግባቡ የተደራጃ አለመሆንና ለማግኘት አስቸጋር መሆን
- በመረጃ መጥፋት የአሽከርካሪዎች/የተገልጋይ/ ምልልስና እንግልት መኖር
- በጥፋት ድግግሞሽ ምክንያት እየጨመሩ የሚሄዱ የከባድ ተሽከርካሪና ዲሲፒልን ቅጣቶችን ለማስፈጸም የተደራጀ መረጃ ማግኘት አለመቻል
- የትራፊክ ቅጣት ወለድ ሲበዛባቸዉ ጠፋብን በማለት አዲስ መንጃ ፍቃድ የሚያወጡ አሽከርካሪዎችን ለመቆጣጠር የሚያስችል የተደራጀ መረጃ ስርዓት  አለመኖሩ
- የከስ ፓድ የጠፋባቸውን አሽከርካሪዎች ቀሪ መረጃ ለማግኘት አስቸጋሪ መሆኑ
- የመረጃ ክፍል መረጃ አያያዝ ለብልሹ አሰራር የተጋለጠ መሆንና እና ለቁጥጥር አመቺ  አለመን
- የመረጃ ክፍል አገልግሎት አሰጣጥ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ባለመሆኑ ለተገልጋዮች ቀልጣፋ፣ጊዜ ቆጣቢና ፈጣን አገልግሎት መስጠት ባለመቻሉ የቅሬታ ምንጭ መሆኑ

- ባለስልጣን ጽ/ቤቱ ከቅ/ፅ/ቤቶች የትራፊክ ደንብ ጥሰትን በተመለከተ አስቸኳይ መረጃ ሲፈልግ በቀላሉ ማግኘት አለመቻሉ (የገቢ፤ የከባድ ተሽከርካሪ፤ የፍጥነት ቁጥጥር ሪፖርቶች--ወዘተ)
- ባለስልጣኑ ከትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጋር ተያይዞ የሰራቸዉን ስራዎች በቀላሉ ለሚዲያና ለሚመለከታቸዉ አካላት መረጃ ለማድረስ የተደራጀ መረጃ አለመኖር
- በተለያየ ምክንያት ከትራፊክ ቁጥጥር ባለሙያዎች እጅ የሚጠፉ ደረሰኞችን ለመቆጣጠር የተደራጀ መረጃ አለመኖር
- .ከትራፊክ ቁጥጥር ጋር ተያይዞ የቅ/ጽ/ቤቶችን አፈጻጸም ለመከታተል የሚያግዝ መረጃ በተደራጀ መልክ አለመኖር
- በተደጋጋሚ የደንብ ተላላፊዎች የሚፈፀሚባቸው ቦታዎችን  በቀላሉ ለይቶ ልዩ ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል መረጃ  ለማግኘት አለመቻል

## 2.3. በተቋሙ ከለውጡ በፊት የነበሩ አስቻይ ሁኔታዎች

- የከተማ አስተዳደር አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ ታግዘው እንድሰጡ የያዘው አቅጣጫና ፍላጎት ጠንካራ መሆን
- የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን ጽ/ቤት የተገልጋይን እንግልትና መጉለላት ለመቀነስ አገልግሎት በቴኪኖሎጂ ተደግፈው እድሰጡ ከማደረግ አንፃር እየተሰሩ ያሉ ስራዎች መኖራቸው
- በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት አሰጣጥ ፊላጎት በተገልጋዮች ዘንድ መኖር
- አንዳንድ ባለሙያዎች ቴክኖሎጂን የማበልፀግና የመጠቀሚ  ተነሳሽነት መኖር

## 2.4. ከለውጡ በፊት የነበሩ ስጋቶች

- ለቴኪኖሎጂ አጠቃቀም ብቁ የሆኑ የተሸሴ ክፍያ ፍላጋ ስራ መልቀቅ
- የሲስቴም መቆራረጥ መኖር
- አንዳንድ ባለሙያዎች በቴክኖሎጂ በመጠቀም አገልግሎትን መሰጠትን እንደተጨማሪ ስራ በመውሰድ መረጃ ወደ ሲስተም ለማስገባት ፍላጎት ማጣት
- በመዋቅር ጥናት ምክንያት ቦታው የተመደበ ባለሙያ ቶሎ ቶሎ መቀያየር
- የግብዓት እጥረት መኖር

# ክፍል ሶስት

## 3. በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ለውጥ ለማምጣት የነበረው አስተሳሰብ

## 3.1. ቅድመ ለዉጥ አስተሳሰብ

### 3.1.1. በአመራሩ ዘንድ የነበረ ለዉጥ አስተሳሰብ

በባለስልጣኑ ቅ/ጽ/ቤት የመረጃ መመዝገቢያ ሲስተሙ ከመበልጸጉ በፊት አመራሩ ላይ በመረጃ አያያዝ ያሉ ችግሮችን ለመቅረፍ ፍላጎት ቢኖርም ግብዓት ለማሟላትና ያሉትን ባለሙያዎች አሳምኖ ወደ ስራ ለመግባት በአመራሩ ዘንድ ስራውን ከባድና በራስ አቅም ልፈፀም አይቻልም የማለት እሳቤ በመኖሩ ጠንካራ ቁርጠኝነት አለመኖር ፡፡

### 3.1.2. በመረጃ ባለሙያዎች ዘንድ የነበረ ለዉጥ አስተሳሰብ

ከአዲሱ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለዉጥ /BPR/ ጥናት በፊት በቅ/ጽ/ ቤቶች የመረጃ ባለሙያ የሚባል የስራ መደብ ያልነበረ በመሆኑ በመረጃ ባለሙያነት ተመድቦ የሚያሰሩት የቴክኖሎጂ እውቀት የሌላቸውና የተለያየ ሙያ የተማሩ ባለሙያዎች ስለሆነ የመረጃ ባለሙያዎች ሆነው ስሰሩ አገልግሎትን በቴክኖሎጅ አስደግፎ መስጠት የተለየ ችሎታ የሚጠይቅ ስለሚመስላቸዉ ቀና የሆነ አመለካከት አለመኖርና ስራው ከሩቁ የመፍራት አስተሳሰብ ጎልቶ ይስታዋል ነበር፡፡

### 3.1.3. በተገልጋዮች ዘንድ የነበረ ለዉጥ አስተሳሰብ

አገልግሎት ለማግኘት ወደ ቅ/ጽ/ቤቱ የሚመጡ ተገልጋዮች የተደራጀ መረጃ ባለመኖሩ ምክንያት የሚደርስባቸዉን እንግልትና መጉላላት በአብዛኛዉ የቅሬታ ምንጭ የነበረ በመሆኑ አገልግሎት እንድት በወረቀት ይሰጣል ዘመኑን የዋጀ በቴክኖሎጅ ተደግፎ አገልግሎት አሰጣጥ መኖር እንዳለበት በተ,ደጋጋም ሀሳብ በማቅረብ ለቴክኖሎጂ ያላቸው ፍላጎት ያንፀባርቁ ነበር ፡፡

## 3.2. በለዉጥ ትግበራ ሂደት የነበረ አስተሳሰብ

### 3.2.1. አመራሩ ዘንድ የነበረ አስተሳሰብ

በለዉጥ ትግበራ ሂደቱ ወቅት አመራሩ አገልግሎቱ በቴክኖሎጅ ተመዝግቦ በመሰጠቱ የመጣውን ለውጥና እየተቀረፈ ያለዉን ችግር በበጎ አመለካከት በመረዳት አልፎ አልፎ የሚታዩ ክፍተቶችን በመጠቆምና የዕለት ተለት ድጋፍና ክትትል በማድረግ ቴክኖሎጅዉ የበለጠ እንዲዳብር የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

## 3.2.2. የመረጃ ባለሙያዎችዘንድ የነበረ አስተሳሰብ

የመረጃ ክፍል ባለሙያዎች መጀመሪያ ከነበረዉ ቴክኖሎጂን በበጎ አመለካከት አለመረዳት በጊዜ ሂደት እየተሸሻለ በተለይም ደግሞ በፊት የነበረዉን ወረቀት ላይ የተመሰረተ መረጃ አያያዝ በማስቀረቱ የተገልጋዮች ቅሬታዎች በቀላሉ መቅረፍ በመቻሉ ደስተኛ ናቸዉ፡፡

### 3.2.3. ተገልጋዮች ዘንድ የነበረ አስተሳሰብ

በቅ/ጽ/ቤቱ ቴክኖሎጂንን በመጠቀም አገልግሎት አሰጣጡ ስለተሻሻለ ተገልጋዮች ከአሁን በፊት ሰሌዳ መቼ፤ በማንና የት ቦታ እንደተፈታ መረጃ በመፈለግ እንዲሁም ፓድ ሲጠፋባቸዉ ኮፒ ለማድረግ መረጃው መቼ ወደ ቅ/ጽ/ቤቱ ገቢ ሆኖ

እንደተመዘገቡ በቀላሉ ለማግኘት ይቸገሩ ነበር፡፡ በሲስተም መጠቀም በመቻሉ በአጭር ጊዜ አገልግሎት ማግኘት በመቻላቸው እርካታቸው አድጓል፡፡

## 3.3.ድህረ ለዉጥ አስተሳሰብ

### 3.3.1. ድህረ ለዉጥ በአመራሩ ዘንድ የነበረ የአስተሳሰብ

የትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች መረጃ መመዝገቢያ ሲስተም ወደ ስራ ከገባ በኋላ መረጃዎች ተደራጅተዉ በመገኘታቸዉ በቀላሉ ከተገልጋዮች ይቀርቡ የነበሩ ቅሬታዎችን መልስ መስጠት በመቻሉ አመራሩ ትኩረት በመስጠት ግብዓት በማሟላት ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ስራው ትኩረት እንዲሰራ አድርጓል፡፡

### 3.3.2. የመረጃ ባለሙያዎች ዘንድ የነበረ የ አስተሳሰብ

የቅርንጫፉ የመረጃ ባለሙያዎች ከተገልጋይ ይደርስባቸዉ የነበረዉን አላስፈላጊ ስድብና ንትርክ ማስቀረት በመቻሉ እንዲሁም በፊት ተገልጋይ በሚመጣበት ወቅት በወረቀት ላይ በተደጋጋሚ በመጻፍ ይፈጠርባቸዉ የነበረዉን መሰላቸትና መረጃ ለማግኘት ወረቀት ላይ በመፈለግ የምባክነው ጊዜ በመቀነሱ ስራው በከፍተኛ በፍላጎት እና ተነሳሽነት እንድሰሩት ከማድረግ ም በተጨማሪ መረጃዎችን በማደራጀት እና በመተንተን ለጥናትና ምርምር ግብዓት በሚሆን መልኩ ማስቀመጥ ችሏል፡፡

### 3.3.3. ተገልጋዮች ዘንድ የነበረ የ አስተሳሰብ

ከትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች ጋር ተያይዞ የሚሰጡ አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ ተደግፎ መስጠት ከተጀመረ በኋላ አገልግሎት የሚያገኙበት ጊዜን ማሳጠር በመቻሉና መረጃን በቀላሉ ማግኘት በመቻላቸው ምክንያት የተገልጋዮች ቅሬታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ እና እርካታቸው እንድያድግ አድርጓል ፡፡

# ክፍል አራት

## 4. ከምርጥ ተሞክሮው የተገኘው ውጤት

### 4.1. ከተገልጋይ አንጻር

- አሽከርካሪዎች የቅጣት ወረቀት ሲጠፋባቸዉ የእርምት እርምጃ የወሰደባቸውን ትራፊክ ተቆጣጣሪ ባለሙያ በመፈለግ ወይም ከንብረት ክፍል ሰነድ ለማስፈለግና ኮፒ ለማድረግ የሚደርሰውን የጊዜ ብክነትን ማስቀረት አስችሏል።
- አገልግሎት ፈላጊዎች ፈጣንና ጊዜ ቆጣብ አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ ብልሹ አሰራርን እንዲቀንስ አድርጓል።
- ተገልጋዮች ስለጠፉባቸዉ መረጃዎች (ሰሌዳ ወይም መንጃ ፈቃድ) ሲጠይቁ በቀላሉ መረጃ ማግኘት መቻላቸዉ።

### 4.2. ከመረጃ ባለሙያዎች አንጻር

- የመረጃ ባለሙያዎች የደንብ ተላላፊዎችን መረጃ ለመመዝገብም ሆነ ለደንብ ተላላፊዎች ለመመለስ የሚጠቀሙት ወረቀት ነክ ሲሆን ይህ አካሄድ ተገልጋዩ አገልግሎቱ በስታንዳርዱ ከተቀመጠዉ ጊዜ በላይ እንዲጠብቁ የሚያደርገው ችግር መቅረፍ አስችሏል፡፡
- የመረጃ ክፍል ባለሙያዎች የሰሩት ሪፖርት ግልፅ እና ታዓማንነት ያለው እንዲሆን አድርጓል፡፡
- በመረጃ ክፍል አገልግሎት አሰጣጥ ፈጣን እንዲሆን ከማድረጉ ባለፊ ተገልጋዮች በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ይነሱ የነበሩ ቅሬታዎች መቀነስ አስችሏል።

### 4.3. ከባለድርሻ አካላት አንጻር

- ከተቋሙ መረጃ የሚፈልጉ ባለድርሻ አካላት ተዓማንነት ያለው መረጃ በቀላሉና በጥራት እንዲያገኙ አስተዋጾ አድርጓል ።

### 4.4. ከባለስልጣን መ/ቤቱ አንጻር

- መንጃ ፈቃድ ጠፋብን ለሚሉ ተገልጋዮች መረጃ በአጭር ጊዜ ውስጥ በማጣራት ምላሽ መስጠት አስችሏል።
- የደንብ መተላለፍ የተቀጡ ቅጣታቸዉን በወቅቱ ባለመክፈላቸዉ ወለድ ላለመክፈል የአሰራር ክፍተት በጠቀም ጠፋብን በማለት ምትክ መንጃ ፍቃድ ለማውጣት የሚፈልጉ አሻከርካዎች መረጃ ለማጠራትና ክፍተቶቹን ለመቆጣጠር አስችሏል።
- የደንብ ተላላፊ አሽከርካሪዎች ክፍያውን እስከወለዱ መሰብሰብ የሚቻልበት ስርዓት መዘርጋት ያስችላል።
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ከትራፊክ ቅጣት መሰብሰብ የሚገባዉን ገቢ መረጃ በቀላሉ ለማግኘት ያግዛል።
- ብልሹ አሰራር እና ሌብነትን ለመቆጣጠር አስችሏል።
- ከባለሙያዎችና አስተባባሪዎች የሚላኩ የደንብ ተላላፊ አሽከርካሪዎች መረጃ ተዓማንነት ለማረጋገጥ ያስችላል ።
- ደንብ ተላላፊ የት እንደተቀጣ፣የተላለፈው የጥፋት እርከን፣ የተሽከርካሪ አይነት፣የመንጃ አይነት እና የመሳሰሉ መረጃዎችን በመተንተን ስራ ላይ ለማዋል አግዟል፡፡

# ክፍል አምስት

## 5. ከምርጥ ተሞክሮ የተገኘው ስኬት

የደንብ ተላላፊ አሽከርካሪዎች መረጃ አያያዝና አደረጃጀት ከወረቀት ነክ በፀዳ መልኩ በቴክኖሎጂ የተደገፈ በመሆኑ መረጃ በፍጥነት አለመገኘት እና አልፎ አልፎ መጥፋት ምክንያት በተገልጋዮች ላይ ይደርስ የነበረውን እንግልትና ከብልሹ አሰራር ምክንያት ይቀርብ የነበረውን ቅሬታ በከፍተኛ ደረጃ ከመቀነስም ባሻገር የተገልጋይ እርካታ እንዲጨምር አስችሎዋል። ከደንብ ተላላፊ መረጃ ወደ መረጃ ክፍል መግባትና መውጣት ጋር ተያይዞ ይነሱ የነበሩ ብልሹ የአገልግሎት አሰጣጥ፣ሌብነትና የባለሙያ ስነ-ምግባር ችግሮች በመፍታት ተገልጋዮች ተገቢውን አገልግሎቶች እንዲያገኙ በማድረግ የተገልጋይ እርካታ እንዲያድግ ከፍተኛ ስኬት በተቋሙ እንዲመዘገብ አድርጓል።

### 5.1. በተቋሙ ስኬት የተገኘበት ዝርዝር ሂደት

- የዳሰሳ ጥናት በማድረግ በተቋሙ የደንብ ተላላፊ መረጃ አያያዝና አደረጃጀት ዙሪያ የነበሩ ችግሮችን የመለየት ስራ ተከናውል ።
- በተቋሙ በደንብ ተላላፊ መረጃ አያያዝና አደረጃጀት ላይ በዳሰሳ ጥናት የተለዩ ችግሮችን ሊፈታ የሚችል ሲስተም የማበልፀገን ስራ በማከናወንና በባለድርሻ አካላት የማስገምገም ስራ ተሰርቷል።
- በተቋሙ ለስራ የሚስፈልጉ ግብዓቶች እንዲሟሉ የማድረግ ስራ ተሰርቷል።
- በሲሰተሙ አጠቃቀም ዙሪያ ያሉት የአመለካከትና ክህሎት ክፍተት ለመቅረፍ የሚረዳ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ለአመራሩና ባለሙያዎች መስጠት ተችሎዋል።
- የትራፊክ ተቆጣጣሪ ባለሙያዎች የተሟላ ደንብ ተላላፊ መረጃ ለዳታ ኢንኮደር ባለሙያዎች በስርዓት እንዲያረክቡ ተደርጓል።
- ዳታ ኢንኮደር ባለሙያዎች የተሰጣቸውን የደንብ ተላላፊ አሽከርካሪዎች መረጃ በሲሲተም ላይ በየእለቱ በሀላፊነትና በተጠያቂነት መንፈስ እንዲመዘግቡ የቅርብ ድጋፍ እና ክትትል በማድረግ የሚስታዋሉ ችግሮችን ቶሎ ቶሎ የመፍታት ስራ ተከናውኗል።
- ወደ ስሲተም የገቡ መረጃዎችን ፍሰት በራሱ በበለፀገው ሲሰተም መቆጣጠር ስራ ተከናውል፡፡
- ለሙከራ በሲስተም ላይ የተመዘገቡ የደንብ ተላላፊ አሽከርካሪዎች መረጃ የመተንተን ስራ ማከናወን ተችሏል፡፡
- የተገኘውን የመረጃ የትንተና ውጤት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመገምገምና የተሰጡ አስተያየቶችን እንግብዓት የመውሰድ ስራ ተሰርቷል።
- ከሚመለከተው አካል የተሰጡ ግብዓቶች/አስተያየቶችን/ በማከል የበለፀገውን ሲስተም ወደ ሙሉ ትግበራ የማስገባት፡፡

### 5.2. የበለፀገውን ሲስተም ለመተግበር ያጋጠሙ ማነቆዎች

- የኢንተርኔት መሰረተ ልማት ዝርጋታ  እጥረት መኖር፤
- የግብዓት እጥረት መኖር/ለምሳሌ ኮምፒዩተር፤
- የቴክኖሎጂ አጠቃቀም እውቀትና ክህሎት ያለው ባለሙያ እጥረት መኖር፤
- በዳታ ኢንኮዲንግ የሰለጠነ የሰው ሀይል አለመኖር፤
- የትራፊክ ቁጥጥር ባለሙያዎች በተሟላ መልኩ የደንብ ተላላፊ አሽከርካሪ መረጃ አለመያዝ፤
- የሙብራት በተደጋጋሚ መቆራረጥ፤
- የኢንተርኔት መቆራረጥ መኖር፤

### 5.3. የበለፀገውን ሲስተም ለመተግበር ያጋጠሙ ማነቆዎች የተፈቱበት አግባብ

- ተቋሙ ያለው ግብዓት አቻችሎ በመጠቀም፤
- በቴክኖሎጂ አጠቃቀም የተሻሉ ባለሙያዎችን ወደ ቢሮ በመሳብ በውክልና በማሰራት፤
- የትራፊክ ባለሙያዎች የተሟላ መልኩ የደንብ ተላላፊ አሽከርካሪዎችን መረጃ እንዲይዙ እና የተጠያቅነት ስርዓት በመዘርጋት፤
- በሙብራት መቆራረጥ የሚፈጠረውን ችግር ለመፈታት ባለህንፃው ጀነሬተር እንዲያዘጋጁና ሙብራት ሲጠፋ ወዲያው እንዲያስነሱ በማድረግ ችግሩ የመቅረፍ ስራ በመስራት፤
- የኢንተርኔት መቆራረጥ በቶሎ ለሚመለከተው በማሳወቅ ለማሰራት ተችሏል፤
- በራስ አቅም ኢንተርኔት ከለበት ወለል ወደ ሌላ ወለል በመውሰ

# ክፍል ስድስት

## 6. የደንብ ተላለፊ ስሲተም በማበልፀግ የተሳሳፉ አካላትና የተጫወቱት ሚና

### 6.1. የመንገድ ትራፊክ ደንብ ማስከበር ዳይሬክተር የነበረው ሚና

የጉለሌ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን የመንገድ ትራፊክ ደንብ ማስከበር ዳይሬክተር በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የደንብ ተላላፊ አሽከርካሪዎች መረጃ አያያዝና አደረጃጀት እንዲሁም ለአሽከርካሪዎች በሚሰጠው አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ በተገልጋዮች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መነሻ በማድረግ መረጃ በመሰብሰብ ፣ በመተንተንና የዳሰሳ ጥናት በማድረግ መረጃ አያያዝ እና አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመለየትና ያሉትን ክፍተቶች ለመፍታት በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት መስጠት ወቅቱ የሚፈልገው የመፍትሔ ሀሳብ ቀርቦ ስራ እንዲጀመር አድርጓል ።

### 6.2. የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጂ የነበራቸው ሚና

በድንብ ተላላፊ መረጃ አያያዝና አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ በተደረገው የዳሰሳ ጥናት የተለዩ ክፍተቶች መነሻ በማድረግ ክፍተቶቹን ለመፍታት የቀረበው የመፍትሄ ሃሳብ ወደ ተግባራ እንዲገባና በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት እንዲሰጥ ያላቸውን ሙያዊ አበርክቶ ከማድረግ ጀምሮ ለስራው የሚያስፈልገውን ግብዓት በማሟላትና የተሻለ የቴክኖሎጂ እውቀትና ለስራው ተነሳሽነት ያለው ባለሙያ ከመደበኛ ስራው ጎን ለጎን ይኸንን ሲስተም እንዲያበለፅግ ሙሉ ሀላፊነት በመስጠት ስራው እንስጀመረው በቅርበት በመደገፍ የተጫወቱት ሚና በእጅጉ የላቀ ነው።

### 6.3. የባለሙያ ሚና

በደንብ ተላላፊ መረጃ አያያዝ አገልግሎት ዙሪያ በተደረገው የዳሰሳ ጥናት የተለዩ ክፍተቶች መነሻ በማድረግ ክፍተቶቹን ለመፍታት የቀረበው የመፍትሄ ሃሳብ ወደ ስራ ገብቶ በመረጃ አያያዝ እና አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚስታዋሉ የነበሩ ብልሹ አሰራር ችግሮች እንዲፈቱ የመረጃ አያያዝና አገልግሎት አሰጣጥ በቴክኖሎጂ እንዲሆን ስራውን አምኖ ከመደበኛ ስራው ጎን ለጎን ከስራ ቀናት ውጪና በበዓላት ቀን ጭምር በሀላፊነትና በተቆርቋርነት መንፈስ የመረጃ መመዝገቢያ ሲስተም ከማበልፀግ እስከ ትግበራ ተጨማሪ ሙያዊ ሀሳቦችን በመቀበልና በእለት ተእለት ስራው የሚገጥሙትን መሰናከሎች በማለፍ የመጣውን መሻሻልና ለውጥ በማስገምገም ሙሉ በሙሉ ውጤታማነቱ ተረጋግጦ እውን እስኪሆን ድረሰ የላቀ ሚና ተጫውቷል፡፡

### 6.4. የሌሎች ባለድርሻ አካላት ሚና

የተጀመረው በቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎት አሰጣጥና መረጃ አያያዝ እውን እንድሆ ከማዕከል ጀምሮ እስከ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ ያሉት ባለድርሻ አካላት የበለፀገው ሲስተም የሙከራ ስራ በተከታታይ በመከታተል ሙያዊ ድጋፍና ክትትል ስራን በቅርበት በማከናወን የበለፀገው መረጃ መመዝገቢያ ሲስተም ምርጥ ተሞክሮ አንድቀመር ለሎች ተመሳሳይ አገልግሎት በመስጠት ላይ ወደሚገኙ ፲፩ዱም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይህ ተሞክሮ እንድሽጋገር ከተማ አስተደደሩና ባለስልጣኑ ቀደም ብሎ የጀመረው ቴክኖሎጂን መሰረት ያደረገ የአገልግሎት አሰጣጥ በመተግበር በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚስታዋሉን ችግሮችን በመፍታትና የህብረተሰቡን እርካታ ለማሳድግ ያበረከቱን አስተዋኦ ዛሬ የበለፀገው መረጃ መመዝገቢያ ሲስተሙ ለደረሰበት ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ ናቸው።

# ክፍል ሰባት

## 7. ተሞክሮውን እውን እንዲሆን ሊከናወኑ የሚገቡ ተግባራት

### 7.1. የበለፀገው ሲስተም ክፍሎች

1. ጎግል ፎርም
2. ጎግል ስፕሪድ ሽት

ጎግል ፎርም ፡ ማለት በመረጃ ክፍል (ዳታ ኢንኮደር) ባለሙያዎች የሚሟላ መረጃዎች የሚገኝበት ከጎግል ድራይቭ የሚገኝ ሲሆን ይህም በቀጥታ ወደ ጎግል ስፕሪድ ሽት ለመመዝገብ ይረዳል፡፡መረጃ በዳታ ኢንኮደር (data encoder) በጎግል ፎርም ኢንኮድ በሚደረግበት ጊዜ ሁለት አይነት መጠይቆች አሉ

1. መጠይቆቹ ግዴታ ምላሽ የሚያስፈልጋቸው፡ እነዚህ አይነት መጠይቆች ከጥያቄዎቹ በቀኝ በኩል በቀይ ኮከብ( * ) ምልክት ኣለው።
2. መጠይቆቹ ግዴታ ምላሽ የማይጠይቁ ናቸው።

- የትራፊክ ቁጥጥር ባለሙያዎች የደንብ ተላላፊዎችን የተያዘ መረጃ ( የመንጃ ፈቃድ ወይም ሰሌዳ ) ለመረጃ ክፍል ባለሙያዎች ያስረክባሉ
- የመረጃ ክፍል ባለሙያዎች ከትራፊክ ቁጥጥር የተረከቡትን መረጃዎች ወደ ጎግል ፎርም መረጃዎችን ይመዘግባሉ በመቀጠልም submit the response ሚለውን በመጫን መረጃውን ወደ ጎግል ስፕሪድ ሽት በቀጥታ ይገባል፡፡

ጎግል ስፕሪድ ሽት ፡ ከጎግል ድራይቭ የሚገኝ ኤክስኤል ሲሆን ይህም ከማይክሮ ሶፍት ኤክስኤል የሚለየው የጎግል ድራይቭ መረጃው በተመሳሳይ ሰዓት እና በተለያየ ቦታ በተለያዩ የሲስተም አጠቃቀም ደረጃ መጠቀም ይቻላል ፡፡ የሲስተም አጠቃቀም ደረጃዎች 4 (አራት) ሲሆኑ ፡

#### 7.1.1. ባለቤት (Owner) ፡

ሙሉ በሙሉ ሲስተሙን የማስተዳደር ስልጣንና ሀላፊነት ያለው አካል ሲሆን አዘጋጅ (Editors)፣ አስተያየት ሰጪ (Commentator) እና ለማንበብ ብቻ የተፈቀደ (Read-only) ተጠቃሚዎችን የማስገባትና የመቀነስም በተጨማሪም አውቶማቲክ የመረጃ ትንተና ሪፖርቶችን ማግኘት የሚችል አካል ነዉ፡፡

#### 7.1.2. አዘጋጅ (Editors) ፡

ይህ አካል በሲስተሙ ባለቤት (Owner) ፍቃድ የተሰጠው ሲሆን በዳታ ኢንኮደሮች የተመዝገበው ወደ ጎግል ስፕሪድ ሽት የገቡ መረጃዎችን የማጥፋትና የማስተካከል ሲሆን በተመሳሳይ የገቡትን መረጃዎች ማውረድ (download ) የሚችልበት ነው።

#### 7.1.3. አስተያየት ሰጪ (Commentator) ፡

ይህ አካል በሲስተሙ ባለቤት (Owner) ፍቃድ የተሰጠው ሲሆን ሀላፊነቱ በዳታ ኢንኮደሮች ተመዝግበው ወደ ጎግል ስፕሪድ ሽት የገቡ መረጃዎች ላይ አስተያየት መስጠት የሚችል አካል ነው።

#### 7.1.4.ለማንበብ ብቻ የተፈቀደ (Read-only) ፡

ይህ አካል በሲስተሙ ባለቤት (Owner) ፍቃድ የተሰጠው ሲሆን ሀላፊነቱ በዳታ ኢንኮደሮች ተመዝግበው ወደ ጎግል ስፕሪድ ሽት የገቡ መረጃዎችን እድያነብ ( እንድመለከት) የተፈቀደለት ብቻ ነው፡፡

## 7.2. የሲስተሙ ተጠቃሚዎች ተግባርና ሀላፊነት

### 7.2.1. የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ዝርዝር ተግባራት

- ለስራው የሚስፈልጉ ግብዓቶችን ማሟላት፤፤
- በቴክኖሎጂ የተሸለ እውቀትና የመስራት ፍላጎት ያላቸው ባለሙያዎችን መለየት፤
- ዳታ ለማስገባት ለተለዩ ባለሙያዎችን በበለፀገው መረጃ መመዝገቢያ ሲስተም ዙሪያ የአቅም ግንባታ/ የግንዛቤ ማስጨበጫ/ ስልጠና መስጠት፤
- ከተጠቃሚዎች ጋር መወያየትና ስምምነት ላይ መድረስ፤
- ጠንካራ ድጋፍና ክትትል ስርዓት መዘርጋት፤
- አፈፃፀሙን መከታተል፣መደገፍና በየጊዜው መፈተሽና መገምገም፤

#### 7.2.2. የመንገድ ደህንነት ግንዛቤ እና ደንብ ማስከበር ዳይሬክተር (Owner) ፡

- የሲስተሙ ተጠቃሚ የሚሆኑትን አካላት የማስገባትና የመቀነስም ተግባር ያከናውናል፣
- የሲስተሙ ተጠቃሚዎችን ይቆጣጠራል፣
- ወደ ሲስተሙ የገቡትን መረጃ መሰረት በማድረግ ሪፖርት ይሰራል፣
- የዳስሳ ጥናት ያከናውናል፣
- ከዳስሳ ጥናቱ በመነሳት የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫ ያመላክታል፣

#### 7.2.3. የትራፊክ ደንብ ማስከበር ቁጥጥር ቡድን ስራዎች አሰተባባሪ (Editors)፡

- መረጃ መዝጋቢዎች(ዳታ ኢንኮደሮች) መረጃ ሲመዘግቡ የተሳሳቱትን ያርማል ፣
- በሲስተሙ ላይ የተመዘገቡ መረጃዎችን ትክክለኛነት ይቆጣጠራል፣
- ለትራፊክ ቁጥጥር የተዘጋጀዉ የክስ ፓድ ለህጋዊ ስራ ብቻ መዋሉን ይቆጣጠራል፣
- በጥፋት ድግግሞሽ ምክንያት እየጨመሩ የሚሄዱ የከባድ ተሽከርካሪና ዲሲፕሊን ቅጣቶችን የድግግሞሽ ብዛት ይለያል፣

#### 7.2.4. የዳታ ኢንኮደር ባለሙያ ተግባራት (Commentator)

- የደንብ ተላላፊ አሽከርካሪዎችን መረጃ ወደ ሲስተም ማስገባት(ያስገባል)፣
- ያልተሟላ የመንገድ ትራፊክ የደንብ ተላላፊ መረጃ አሽከርካሪዎች ሲመጡ በአስተያየት መፃፍያ(Dialog Box) ላይ የተጓደሉትን መረጃዎች ይፅፋሉ፣

#### 7.2.5. የትራፊክ ተቆጣጣር ባለሙያዎች ተግባራት

- የመንገድ ትራፊክ ደንብ ተላላፊ አሽከርካሪዎችን መረጃ በተሟላ መልኩ በመያዝ በበለፀገው ሲስተም መረጃ መመዝገቢያ ላይ ለሚያስገቡት ዳታ ኢንኮደር ባለሙያዎች ያስረክባሉ፡፡

## ክፍል ስምንት

### 8. ሌሎችተቋማት ሊማሩትየሚገባ ቁም ነገር

- በቴክኖሎጂ የተደገፈ መረጃ አያያዝ መረጃው ተዓማንነት እንዲኖረው በማድረግ ተጋልጋይን በፍጥነት ጊዜ ቆጣብ በሆነ መንገድ ለማስተናገድና አገልግሎት ለመስጠት ያለው ጠቀሜታ የጎላ መሆኑን ሊገነዘቡት ይገባል፣
- በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት አሰጣጥ የከተማችን ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ካለው የጎላ ፋይዳ በተጨማሪ በተቋማት ውስጥ የሚታየውን የተጋልጋይን እንግልት፣ ምልልስና ብልሹ የአገልግሎት አሰጣጥን በመቅረፍ የተገልጋይን እርካታ ለማሳደግና በተገልጋዮች በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታ በመሰረታዊነት ለመቀነስ ያለውን አስተዋጾ የላቀ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፣
- ተቋማት የተቋማቸውን ስትራቴጂክ አቅድ አፈፃፀም በዳሰሳ ጥናት በማድረግ ያላቸውን ጥንካሬ እና ክፍተቶችን በራስ አቅም በመለየት የታዩ ክፍተቶችን ለመቅረፍ ስልት በመንደፍ መስራት ወይም የተሻለ እቅድ አፈፃፀም ከላቸው ሌሎች ተቋማት ምርጥ ተሞክሮ በማምጣት ከራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም አላምዶ ቢተገብሩ ለተሻለ ውጤትና ስኬት የሚያበቃ መሆኑን ትምህርት ሊወሰወዱበት ይገባል፣

# ክፍል ዘጠኝ

## 9 መደሚደምያ እና ማጠቃለያ

### 9.1 የምርጥ ተሞክሮ ቀማር ኮሚቴ ምክረ ሀሳብ

- የአዲስ አበባ ከተማ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን የተቀመረውን ምርጥ ተሞክሮ ወደ ሌሎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በማስፋት የትራፊክ ደንብ ተላላፊ አሽከርካሪዎች የመረጃ አያያዝ እና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት እንዲሻሻል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤
- ባለስልጣኑ የበለፀገውን መረጃ መመዝገቢያ ሲስተም ለመጠቀም የሚያስችል የኢንተርኔት አገልግሎት በሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲኖር ምቹ ሁኔታ ቢፈጥር፤
- በሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚገኙ የመረጃ ባለሙያዎች የበለፀገው ሲስተም አጠቃቀም ክህሎት ስልጠና የሚያገኙበት እድል ቢመቻች፤
- ባለስልጣኑ ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት በመዘርጋት ተቀምሮ የተስፋፋው ምርጥ ተሞክሮ ትግበራና አፈፃፀም መከታተያ ስርዓት መዘርጋት ቢችል፤
- የመረጃ መመዝገቢያ ቋት ሲሞላ በስራ ላይ ሚፈጠረውን መስተጓጎል ለመቅረፍ ከወዲሁ ተጨማሪ የመረጃ ማኖሪያ(Storage) ወደ መጠባበቂያ(Backup)መውሰድ የሚቻልበት ታሳቢ ያደረግ ስራ ቢሰራ፤
- ሌሎች የአገልግሎት አሰጣጦችም በቴክኖሎጂ የተደገፉ እንዲሆኑ በራስ እቀም ቴክኖሎጂን አበልፅጎ መጠቀም ላይ በቀጣይም በትኩረት የሚሰራበት ሁኔታ ለማጠናከር የቴክኖሎጂ እውቀትና ችሎታ ያላቸው ባለሙያዎች መጠቀም ላይ በትኩረት ቢሰራበት
- ይህን የተቀመረውን ምርጥ ተሞክሮ ወደ ሌሎች መሰል ተቋማት(ትራንስፖርት ቢሮ እና ትራፊክ ፖሊስ መምሪያዎች) ማስፋት የሚቻልበት ሁኔታ ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት በቀጣይ የሚሰፋበት ሁኔታ ቢመቻች።

### 9.2.-መደሚደምያ

አገራችን ኢትዮጵያ እንደ ሀገር በአፍሪካ አህጉር ብሎም በአለም ላይ ተወዳዳሪ ለመሆን እና ቀጣይነት ያለዉ ፈጣን ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዕድገት ለማስመዝገብ ቴክኖሎጂ መር የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት ለማጎልበት አቅጣጫ ቀይሳ ወደ መሬት ለማዉረድ ጥረት በማድረጓ ለውጥ ማየት የጀመረች መሆኑ ይታወቃል፡፡ አዲስ አበባ ከተማ እንደ ኢትዮጵያ ዋና ከተማነቷ እና የብዙ ዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ መቀመጫ እንደ መሆኗ መጠን ዘመኑ ወደ ደረሰበት የእድገት ማማ ለመውጣት የነዋሪውን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ከማሻሻል ጎን ለጎን ለነዋሪው የሚሰጡ አገልግሎቶች ቀልጣፋ፣ጊዜ ቆጣቢና ዉጤታማ እንዲሆኑ በቴክኖሎጅ ተደግፈዉ አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸዉ ግልጽ አቅጣጫ አስቀምጣ ወደ ስራ መግባቷ የሚታወቅ ነዉ፡፡

ይህንን የከተማ አስተዳደር የያዘውን በቴክኖሎጂ የተገደፈ አገልግሎት መስጠት የተገልጋይን እንግልት፣ምልልስ፣ብልሹ የአገልግሎት አሰጣጥ እና ሌብነት በማስቀረት የተገልጋዮችን እርካታ ለማሳደግ ይቻል ዘንድ የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን ጉለሌ ቅ/ጽ/ቤት የነበረበትን የመረጃ አደረጃጀትና በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የነበሩ ችግር

ለመፍታት በአመራሩ ቁርጠኝነትና ያላሰለሰ ድጋፍና ክትትል እንዲሁም በባለሙያዎች ከፍተኛ ተነሳሽነት የትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች መረጃ መመዝገቢያ ሲስተም(ቴክኖሎጂ) አበልፅገው ወደ ተግባር ማስገባት በመቻሉ በቅ/ጽ/ቤቱ ከደንብ ተላላፊ መረጃ አያያዝና አገልግሎት አሰጣጥ ጋር ተያይዞ ይነሱ የነበሩ ችግሮችን መቅረፍ ተችሏል፡፡ በመሆኑም በመረጃ መመዝገቢያ ሲስተም የተገኘዉን ዉጤት በመቀመርና በማስፋት ሌሎች የባለስልጣኑ ቅ/ጽ/ቤቶች ምርጥ ተሞክሮዉን ከራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥመው በማላመድ እንዲጠቀሙ ቢደረግ እንደ ተቋም ያሉትን የተደራጀ መረጃ አያያዝ ችግር ከመቅረፍ አልፎ ተርፎም ወደ ሌሎች ተቋሞች በማስፋፋት እንደ ከተማ ብሎም እንደ ሀገር የተያዘዉን የቴክኖሎጂ መር የአገልግሎት አሰጣጥና ዕድገት አቅጣጫ እዉን ለማድረግ የሚያግዝ  በመሆኑ ቀጣይ በቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት የተገልጋይን እርካታ ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡

## 9.3- ማጠቃለያ

በአንድ ሃገር ዉስጥ ሁለንተናዊ ዕድገት ለማስመዝገብ የመንግስት ተቋማት ሚና ወሳኝ ነዉ ፤ ምክንያቱም ኢኮኖሚዉን ፣ፖለቲካዉን እንዲሁም ማህበራዊ እንቅስቃሴዉን በእኩልነትና በፍትሃዊነት ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የሚወጡ ህጎችና ደንቦች ወደ መሬት የሚወርዱት ወደ ተግባር የሚገባበት መንገድ ስለሆነ ነዉ፡፡ እያንዳንዱ የመንግስት ተቋም የተቋቋመበትን ዋና ተልዕኮ ለማሳካት የሚሰጣቸዉን አገልግሎቶች ቀልጣፋና ዉጤታማ በማድረግ የተገልጋዩን እርካታ ማሻሻል የህልዉናዉ መሰረት መሆኑ ይታወቃል፡፡ አገልግሎት አሰጣጥን በተለያየ መንገድ ማሻሻል ይቻላል ለአብነት የሰዉ ሃይል፣አደረጃጀት በማሻሻል፣ የግብዓት አቅርቦትን በማሟላት፣የሰዉ ሃይል አቅምን በስልጠና በመገንባት፣ አሰራርና ቴክኖሎጂን በማሻሻልና በመጠቀም ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን የጉለሌ ቅ/ጽ/ቤት በአዲሱ የባለስልጣኑ አደረጃጀት መሰረት ራሱን ችሎ እንደ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከተደራጀ በኋላ የአገልግሎት አሰጣጡን ለማዘመንና የተገልጋዮችን እርካታ ለማሻሻል የነበረዉን የመረጃ አደረጃጀት ችግር መቅረፍ አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት ጥናት ላይ የተመሰረተ መፍትሄ ለማምጣት ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ የተደረገዉ ዳሰሳ ጥናት የመረጃ ግብዓትን ከተልጋዮች በቀጥታ በመቀበል፣ በ2015 የቀረቡትን ቅሬታዎች ሰነድ በመፈተሽ፤ በቅ/ጽ/ቤቱ የመረጃ አያያዝ እና አደረጃጀት የነበረበትን ሁኔታ በአካል በመመልከት እና ሰነዶችን በመፈተሽ እንደመረጃ ምንጭ በመጠቀም ጥናት አከናውኗል፡፡ በዳሰሳ ጥናቱ ችግሩን ለመፍታት የተለያዩ አማራጮችን እንደ ምክረ ሃሳብ ያቀረበ ሲሆን በተለይም ከትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች ጋር ተያይዞ የሚነሳ ቅሬታንና የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓትን ወጪ ቆጣቢ ቴክኖሎጂን በመጠቀም መረጃ ማደራጀት ቢቻል ተገልጋዮች በቅ/ጽ/ቤቱ ላይ የሚያነሱትን ቅሬታ እና በመረጃ ክፍል ሰራተኞች ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን መቅረፍ እንደሚያስችል ለመረዳት ተችሏል፡፡ ስለሆነም የትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች መረጃ መመዝገቢያ ሲስተም ጎግል ድራይቭን በመጠቀም ሲስተሙን አበልፅጎ ወደ ስራ ማስገባት ተችሏል፡፡ ሲስተሙን መጠቀም በመቻሉ የተገልጋዮችን ቅሬታ በመቀነስ፤ ብልሹ አሰራርን በማስወገድ፤ አገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻልና የተደራጀ መረጃ እንዲኖር በማስቻሉ ለውጥ ማምጣት ተችሏል፡፡ ስለዚህ ባለስልጣኑ መስሪያ ቤቱ በጉለሌ ቅ/ጽ/ቤት የበለጸገዉና በተግባር ተፈትሾ ውጤታማነቱ የተረጋገጠውን መረጃ መመዝገቢያ ሲስተም እንደ ምርጥ ተሞክሮ ተወስዶ እንዲቀመርና ወደ ሌሎች የባለስልጣኑ ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲስፋፋ አቅጣጫ በመስጠቱ  ምርጥ ተሞክሮ ለማስፋፋት እንዲያስችል ይህ የምርጥ ተሞክሮ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡

## ዋቢ ጽሑፎች


- የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ የተሸሻለ የቤንችማርኪንግና ምርጥ ተሞክሮ ትግበራ ማስፈፀሚያ ማኑዋል (2014)
- የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ  የምርጥ ተሞክሮ መለያ ፣መቀመሪያና መስፊያ ሰነድ (2006)
- የጉለሌ ቅ/ጽ/ቤትን ሁለንተናዊ ክፍተቶች በመለየት እንደገና ለማደራጀት የተደረገ የዳሰሳ ጥናት ሰነድ (2015)